# እውነተኛ መሪዎች የሚታወቁት በቀውጢ ቀንና ሰዓት በሚወስዱት እርምጃ ነው

ስለ እውነተኛ መሪዎች ክንውን፣ ስለ አመራርና ስለመሪዎች ምርመራና ጥናት ካደረጉ ሊቃውንት ውስጥ ተቀዳሚ ሥፍራ ያላቸውን፤ (Douglas McGregor, Warren Bennis, James MacGregor Burns and John P. Cotter) ጽሑፎች ብንመለከት እውነተኛ መሪዎች ድርጅታቸውን ወይንም አገራቸውን ችግርና መከራ ሲገጥማቸው ጥልቅ የሆነና የሰከነ ግራ ቀኙን የተመለከተ ስሌት አካሂደው አዳኝ መፍትሔ ይቀይሳሉ፤ መፍትሔውንም በፍጥነት ሁናቴ እሥራ ላይ ያውሉታል:: ለውሳኔውና ለመፍትሔው ሙሉ ኃላፊነትንም ይቀበላሉ:: ፕሬዚዳንት ሄሪ ትሩማን በዴስካቸው ላይ "The buck stops here" የሚል ምልክት ያስቀመጡት ይህንን ለመግለጽ እንደሆነ የታወቀ ነው::

በአሁኑ ሰዓተ የቅንጅት ፓርቲ በትልቅ ፈተና ላይ እንዳለ ለሁሉም ግልጽ ነው:: ቅንጅትን ለመከፋፈል፣ ለማዳከምና ብሎም ለማፍረስ ውህደቱ ከመጠናቀቁ በፊት በድርጅት አባልነትና በዳመና ሽፋን ሰርገው በገቡ የወያኔ ወኪሎችና ምንደኞች ትልቅ ዘመቻ እየተካሄደበት ነው:: ዘመቻው የተጀመረው የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ጠቅላላ የሕዝብ ምርጫ ከተካሄደና ወያኔ በማያወላውል ሁናቴ ከተሸነፈ በኋላ መሆኑ አሁን በጣም ግልጽ ሆኗል::

ዘመቻው በዶክተር ብርሃኑ ነጋ ፊታውራሪነት ከቃሊቲ እስር ቤት (?) ሲመራ ቆይቶ፤ ከፍቺ በኋላ ደግሞ ጋሻጃግሬዎቹን ይዞ ወደ አሜሪካና ካናዳ በመዝመት ብዙ የመከፋፈልና የማዳከም ተግባር በማካሄድ ላይ ነው:: ጥቂቶቹንም ለመጥቀስ ያህል፤

- ቅንጅት ብዙ መሪዎች (ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ) እንጂ አንድ መሪ የለውም ብለው ተነገሩ፣ አስነገሩ፤
- ፕሬዚዳንቱን የሌሉበት የሕዝብ ስብሰባ በመጥራት የፕሬዚዳንቱን ሥልጣን የሚጻረር ተግባር ፈጸሙ፤
- በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ጽህፈት ቤት (በስቴት ዲፓርትመንት) ከነልደቱ አያሌው፣ ከነበየነ ጴጥሮስ፣ ከነአየለ ጫሚሶ ጋር ሆነው ታማኝ የወያኔ ተቃዋሚ በመሆን ወደፊት እንደሚሰሩ ስምምነት አደረጉ:: ለዚህም ትብብራቸው የአሜሪካ 20 ሚሊዮን ብር ድጎማ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገባላቸው፤
- ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ለአሜሪካ ኮንግሬስ አባላት በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በእስር ቤት የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ቁጥር ከአንድ መቶ አይበልጥም በማለት ስለወያኔ መንግሥት ጥሩነት መሰከረች፤
- ኢንጂነር ግዛቸው ሺፈራው HR 2003 እንደማያስፈልግና በሕጉ ላይ እንዲፈጸሙ የተጠቀሱት ጉድለቶች ከወያኔ መንግሥት ጋር በዲፕሎማሲ እንደሚፈቱ አስታወቀ፤
- ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ሚኒአፖሊስ፤ ሚኒሶታ ተለጣፊው ቡድን ባዘጋጀላት ስብሰባ ላይ ቅንጅት ስላደረገባቸው የፈጠራ "በደል" የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ጠየቀች፡
- ዶክተር በፈቃዱ ደግፌ መኢአድ ከቅንጅት ሊገነጠል እየተዘጋጀ ነው ብሎ ለጀርመን ሬዲዮ ቃለምልልስ ሰጠ፤
- ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የራሳችንን ቅንጅት ይዘን በየመንገዳችን እንሄዳለን ለየብቻችን እንጓዛለን ብሎ በዘረጋው የፓልቶክ መድረክ አወጀ::

እነኝህ ሁሉ ድርጊቶች ወደ አሜሪካ እንዲመጡ ካደረጋቸው አጀንዳ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም:: ያንን አጀንዳ ፈጽሞ አላከናወኑም:: ለኦፊሴላዊው አጀንዳ እንዳልመጡም ግልጽ ነው::

ይህ ሁሉ የመከፋፈልና የማፍረስ ዘመቻ ሲካሄድ የፓርቲው ፕሬዚዳንት ሕክምና ከማድረግና ጉዳዩን በጽሞና ከመከታተል ሌላ ምንም እርምጃ አልወሰዱም:: ጉዳዩ ያሳሰባችው ብዙ የቅንጅት ደጋፊዎች ለምን አንድ ዓይነት እርምጃ አይወስዱም የሚል ጥያቄ ሳያሰሙ አልቀሩም::

ነገር ግን እውነተኛ መሪዎች ውሳኔ የሚያደርጉት የበሰለ፣ የሰከነ፣ ሚዛናዊና ያልተቻኮለ ምርምርና ጥናት ካደረጉ በኋላ ስለሆነ፤ የክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ውሳኔም ይህን ፈር የተከተለ ነው:: ጊዜውና ሰዓቱ ሲደርስ ቅንጅትን ከሚካሄድበት የመከፋፈልና የማፍረስ አደጋ ለማዳን ቆራጥ እርምጃ ወሰዱ:: ይህንንም እርምጃ በመውሰዳቸው ያለባቸውን የመሪነት ኃላፊነት ተወጥተዋል::

ይሁን እንጂ የከፋፋዮች ግብረአበሮችና ከፋፋዮች የዘረጓቸው የመገናኛ አውታሮች (ER, Ethiomedia. EMF, Current Affairs, Abugida, Addis Dimts...) ውሳኔውን አወገዙ:: ኮነኑ:: ይህንን ዓይነት ውሳኔ ለማድረግ ፕሬዚዳንቱ ሥልጣን የላቸውም ብለው ተንጫጩ::

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ያልተገነዘቡትና የማያውቁት ቁም ነገር አንድ ድርጅት ወይንም አንድ አገር ቀውጢ ሰዓት ወይንም ቀን (crisis) ሲገጥመው ፕሬዚዳንቱ ድርጅቱን ወይንም አገሩን የማዳንና አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

ይህ ኃላፊነትና ግዴታ በወረቀት ላይ ሰፈረም አልሰፈረም በተውፌትና በልምድ ያለና የተጠበቀ ሥልጣን ነው። ኤክስኪዩቲቭ ኦቶሪቲ (**Executive Authority**) የሚባለውም ይህ ነው። ይህ የሁሉም መሪዎች ሥልጣን ነው። ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልም የቅንጅት መሪ በመሆናቸው ብቻ ይህ ሥልጣን አላቸው። ከዚህም አልፎ በቅንጅት መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ቁልጭ ብሎ መቀመጡ ይፋ ሆኗል። ይህን ዓይነት እርምጃ መውሰድ የማይችል መሪ ለምንስ ያስፈልጋል? የመሪነትስ ትርጉሙና ሥራው ምንድነው? ድርጅቱን ወክሎ የሚናገር የሚወስን ማነው? መልሱ ግልጥ ነው። ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ፓርቲው ፕሬዚዳንት ያደረጋቸው የፕሬዚዳንት ሥራ እንዲሰሩ ነው። አሁን የወሰዱት እርምጃ ከሚጠበቁባቸው ኃላፊነቶች አንዱ ነው።

የፕሬዚዳንቱን ስልጣን ሊሰጥና ሊያነሳ የሚችለው ፓርቲው ብቻ ነው። ይህንንም ለማድረግ ሕግና ሥነሥርዓት አለው። ሕግና ሥነሥርዓቱም የሚከናወነው በዲሞክራሲ መርሆዎች መሠረት ነው። ከዚያ ውጭ ጥቂት የወያኔና የውጭ መንግሥታት ምንደኞች ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው ሊያካሂዱት የሞከሩት መፈንቅለ ሥልጣን የውንብድና ተግባር ነው።

መፈንቅለ ሥልጣን ሊያደርጉ በመሞከራቸው የዲሞክራሲን መርሆዎች የማይቀበሉ ለመሆናቸው የማያጠያይቅ ማስረጃ ሰጥተውናል። የዲሞክራሲን መርሆዎች ሳይከተሉ፣ የፓርቲውን የመሪ አመራረጥ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ፣ የፓርቲው ፕሬዚዳንት ቦታ ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሳይሆንና ሳይታወጅ በመፈንቅለ ሥልጣን ቦታውን ሊይዙ የሚሞክሩ የሥልጣን ጥም ያሳበዳቸው አምባገነኖች ወይም ዲክተተሮች ናቸው። ዲሞክራሲያዊ መሪነት በመፈንቅለ ሥልጣን አይገኝም። ሆኖም አያውቅም።

ቅንጅት የሚታገለው እኮ የአገሪቱ መሪ በጠመንጃና በመፈንቅለ መንግሥት ሳይሆን፣ በሕዝብ ፈቃድና ምርጫ እንዲሆን ነው። ዶክተር ብርሃኑና ግብረአበሮቹ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሳይሆን በመፈንቅለ ሥልጣን ስልት የፕሬዚዳንቱን ሥልጣንና ቦታ ለመንጠቅ በመሞከራቸው የእነሱን ማንነትና እምነት ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። በዚህ ሙከራቸው አሳፍረውናል። ለቦታውም ብቁ እንዳልሆኑ እነሱው በሥራቸው መስክረዋል።

በአገር ቤትም ይሁን በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ መሪዎቻችን ከተፈቱ በኋላ ያ ለወያኔ አቅርበውት የነበረውን ባለ ስምንት ነጥብ መደራደሪያ እንደገና ለወያኔ አቅርበው ውይይትና ድርድር ያካሂዳሉ ብሎ እንጂ ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማፍረስ የውስጥ ጦርነት ይጀምራሉ ብሎ በፍጹም አልገመተም፡ ሊገምትም አይችልም። ምክንያቱም በታሰሩት መሪዎች ላይ ታላቅ እምነት ነበረው። ያንን እምነት ነው እነ ዶክተር ብርሃኑና ግብረአበሮቹ ያፈረሱት። የሕዝብን እምነት ያፈረሰ ሰውም ይሁን ቡድን የሕዝብ ወኪልና ተሚጋች ሊሆን አይችልም።

አንዳንድ የጋዜጠኛነት ፕሮፌሺን ብቃት የሌላቸው የከፋፋዩ ቡድን ፕሮፓጋንዲስቶች ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልን ይህን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ሥልጣን የሰጣቸውን የደንብ አንቀጽ እንዲነግሯቸው ሲጠይቁ ሰምተናል። ጥያቄው የእነርሱን ማንነት አጋለጠ እንጂ የሰራው ፋይዳ የለም። እነኚሁ ጋዜጠ ኞች ነን ባዮችና የፕሮቶኮል ሥነሥርዓት ማወቅ የሚጠበቅባቸው አንድ የሕዝብ ተመራጭ የተከበሩ ወይም ክቡር ተብሎ መጠራቱን እንኳን አያውቁም። ሕዝብ የመረጠውን፣ ሕዝብ ያከበረውን፣ ማንም ሊሽረው ወይንም ሊያቀለው አይችልም። ትልቅም ሰው ሊያቀል የሚሞክር ትንሽ ሰው ብቻ ነው።

ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ይህንን ቅንጅትን የማዳን እርምጃ ባይወስዱ ኖሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያዝንባቸው ነበር። ቅንጅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ምኞት፣ ተስፋ፣ እምነትና ፍላጎት የሚንጸባረቅበት ድርጅትና አርማ ነው። ጥቂት በውጭ መንግሥታትና በወያኔ የተገዙ ከግል ጥቅማቸው ሌላ የአገርና የሕዝብ አጀንዳ የሌላቸው ሰዎች ሊከፋፍሉትና ሊያፈርሱት አይችሉም። በመሞከራቸው አዝነንባቸዋል።

እነ ዶክተር ብርሃኑና ወኪሎቻቸው ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማፍረስ የተጠቀሙት ዘዴ ደግሞ የቅንጀትን አጀንዳ በሚያራምዱ ግለሰቦች ላይ ትልቅ የስም ማጥፋትና ዘለፋ ማካሄድ ነው። በመጀመሪያ ሻለቃ ዮሴፍ ያዘውን ገንዘብ ወሰዱ በማለት የበሬ ወለደ ውሸት ማናፈስ ነበር። ቀጥሎ ደግሞ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትን በሀሰት መወንጀልና ስም ማጥፋት ሆነ። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ

እንደነጠረ ወርቅ መልካም ዝናና ስም ያላቸውን ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልን የማይረባ የአሉባልታ ውንጀላ እያካሄዱባቸው ነው:: እነኝህ ይሉኝታ የሌላቸው የሕዝብና የአገር ጠላቶች ይህን ውሸትና አሉባልታ የሚያናፍሱት ሕዝብ ከቅንጅት እንዲርቅ ለማድረግ ነው:: የጥፋት ዒላማቸው ቅንጅት ነው:: ቅንጅት ካልተከፋፈለ ብሎም ካልፈረሰ ወያኔም ሆነ የሚደግፉት መንግሥታት እንቅልፍ አይወስዳቸውም:: እንደእነርሱ ፕላን የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አጀንዳ የሚያራምድ ድርጅትም ሆነ የድርጅት መሪ ተጠናክሮ ወደፊት መሄድ የለበትም:: በተለይም እንደክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ያለ አገር ወዳድ፣ ቆራጥ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ሰርቶና አሰርቶ ማንነቱን ያስመሰከረ፣ ለግል ጥቅምና ዝና ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከርሃብ፣ ከድህነት፣ ከበሽታ፣ ከድንቁርና፣ ከጭቆናና ከግፍ አስተዳደር ነጻ ለማድረግ ኢትዮጵያም ያጣችውንና በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ እንዲኖራት የሚገባውን ክብርና ማዕረግ እንድታገኝ የሚጥር ሰው እንደጠላት ነው የሚታየው:: ብዙም የስም ማጉደፊያ ቅጥል ይሰጠዋል:: ሆኖም ግን ይህንን የስም ማጉደፍና ማጥፋት በሕዝብ መድረክ መረጃ አቅርበው አያሳምኑም:: ያለቸው መድረክ ያረቄ ቤት ባንኮኒና የፕሮፓጋንዲስቶቻቸው ድኅረ ገጾች ናቸው:: በምዕራቡ አገሮች አንድ ሰው ወንጀሉ በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ነጻ ነው:: ወያኔና እነርሱ ብቻ ናቸው መጀመሪያ ወንጀለኛ ነህ ካሉ በኋላ አሁን ወንጀለኛ አለመሆንክን አሳምን የሚሉት:: እነኚህ ናቸው ታዲያ ኢትዮጵያ ውስጥ የህግ የበላይነት ስነስርዓት የሚያመጡ? ወይም እንዲመጣ የሚታገሉት? አይደሉም:: ሊሆኑም አይችሉም::

ይሁን እንጂ የቅንጅትና የኢትዮጵያ ሕዝብ የዲሞክራሲ ሠላማዊ ትግል ተጠናክሮና ወደፊት መሄድ አለበት:: ግቡንም እንደሚመታ ምንም ጥርጣሬ የለም:: ይህም ሰላማዊ የዲሞክራሲ ትግል ወደፊት የሚሄደውና ግቡን የሚመታው በክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል መሪነት እንደሆነ አያጠራጥርም:: ለወራት በአሜሪካ ሲያደርጉ የቆዩት ሕክምና በመጠናቀቅ ላይ በመሆኑ በቅርቡ በአሜሪካና በካናዳ ከተሞች በመዘዋወር ለቅንጅት ደጋፊዎችና ለመላው ኢትዮጵያዊ ንግግር እነደሚያደርጉ ይጠበቃል፣ ውይይትም ያካሂዳሉ:: በእነዚህ ንግግሮችና ውይይቶች ደጋፊውና ኢትዮጵያዊው ሕብረተሰብ ከፕሬዚዳንቱ ሊሰማ የሚፈልጋቸው ጉዳዮች እንዳሉ ይታመናል:: ከዚህ ቀጥለው የተጠቀሱት ነጥቦች እንደሚኖሩባቸው ይገመታል፤

- የቅንጅት የወደፊት ሂደትና አጀንዳ ምን እንደሚመስልና በውጭ ያለው ደጋፊና ሕብረተሰብ ሊያደርግ የሚገባው አስተዋጽኦ እና ተሳትፎ፤

- እስካሁን የታየው ቅንጅትን የመከፋፈልና የማዳከም እንቅስቃሴ በአስቸኳይ ተከታታይ እርምጃ እንዲወሰድበትና ከእንግዲህ ወዲያም ቅንጅት ለእንዲህ ያለ አደጋ እንደማይጋለጥ ማስተማመኛና ተስፋ እንዲሰጠው፤

- የከፋፋዮች ወኪሎችና ካድሬዎች የቅንጅትን ስምና ዓርማ በመጠቀም ብዙ የሕዝብ ማወናበድና ግራ ማጋባት ሥራ ስላካሄዱና በማካሄድም ላይ ስላሉ፣ በቅንጅት ስም ገንዘብም ስለሚሰበስቡ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም ጥብቅ ቁጥር እንዲደረግ፤

- የቅንጅትን እውቅናና ምዝገባ በተመለከተ አስፈላጊው እርምጃ ተወስዶ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ::

ቅንጅት አንድ ነው !
ኢትዮጵያም አንድ ናት!
የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅንጅትን ዓርማ አንግቦ ያሸንፋል!

ወርቁ ሀብተማርያም
ቶሮንቶ፤ ካናዳ